Nationellt centrum mot hedersrelaterat våld och förtryck

Jämställdhetsmyndigheten

Migrationsverket

Polismyndigheten

Myndigheten för stöd till trossamfund

Socialstyrelsen

Åklagarmyndigheten

ለበለጠ መረጃ **konsstympning.se** ይጎብኙ

**konsstympning.se**



# በራስዎ ሰውነት ላይ መወሰን መቻል ሰብአዊ መብት ነው!

**የሴት ግርዛት ምንድን ነው?**
የሴቶች ግርዛት የሴቶችን የብልት የውጪ ክፍል ማስወገድ ወይም መጉዳትን የሚያካትት ነው። በዓለም ላይ በየትኛውም ቦታ ሊከሰት ይችላል ። በአንዳንድ የአፍሪካና የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት በጣም የተለመደ ነው።

የተለያዩ ዓይነት የሴት ግርዛቶች ያሉ ሲሆን ከአንድ ሃይማኖት ወይም ባሕል ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም። የሴቶች ግርዛት በደረሰባት ሴት ላይ ከባድ አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል።

**ሕክምና ወይም ድጋፍ ያስፈልግዎታል?**
ህክምና፣ ድጋፍ ወይም እርዳታ የሚያስፈልግዎት ከሆነ በአካበቢዎ የሚገኘውን ማህበራዊ አገልግሎት፣ የጤና ማእከል ወይም የማህጸን ህክምና ክሊኒክ ያግኙ። ስዊድን ውስጥ የሴት ግርዛት ላጋጠማቸው ሴቶች ህክምና የሚሰጡ ሁለት ስፔሻሊስት የሆስፒታል ክሊኒኮች አሉ ። በSödersjuk-huset ውስጥ የሚገኘው Amelmottagningen ስቶክሆልም ውስጥ እና በAngereds närsjukhus ጉተንበርር ውስጥ የሚገኘው Vulva-mottagningen። ይሁን እንጂ በስዊድን እርስዎ በሚኖሩበት ቦታ ሁሉ እና ምንጊዜም ሕክምናና ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ።

ተማሪ ከሆንሽ ወደ ትምህርት ቤቱ አማካሪ ወይም የተማሪዎች ነርስ መሄድ ትችያለሽ። በተጨማሪም እርስዎም ሆኑ ሌላ ሰው ወንጀል ተፈጽሞብዎት ቢሆን ወይም ሊዘህ ተጋላጭ ከሆኑ ፖሊስ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል።

konsstympning.se

**ለወላጆችና ለቅርብ ዘመዶች**
እርስዎ እንደወላጅ ሴት ልጅዎትን ከማንኛውም አይነት የሴት ልጅ ግርዛት የመጠበቅ ሃለፊነት አለብዎት። እንደ ዘመድ በእርስዎ የቤተበብ ቀለበት ውስጥ ያለች አንድ ሴት ልጅ ምንም አይነት የሴት ልጅ ግርዛት እንደማይደርስባት የማረጋገጥ ወሳኝ የሆነ ሃላፊነት አለብዎት።

እርስዎ የሚያውቋት አንድ ሴት የሴት ልጅ ግርዛት ሊደርስባት ይችላል የሚል ስጋት አለዎት? በእርስዎ የመኖሪያ ሰፍራ የሚገኙ የመንስግት አካላትን ያግኙ (እርስዎ የሚፈልጉ ከሆነ ማንነትዎ እንዳይታወቅ ማድረግ ይችላሉ) ወይም በ114 14 ለፖሊስ መደወል ይችላሉ። ድንገተኛ አደጋ ሲከሰት በ112 ላይ መደወል አለብዎት።

**ሕጉ ምን ይላል?**
በስዊድን ሕግ መሠረት አንድን ሴት መግረዝ ከባድ ወንጀል ነው። የሴት ልጅ ግርዛትን መሞክር፣ ለመሞከር መዘጋጀት ወይም መፈጸምም ከባድ ወንጀል ነው። በተጨማሪም የሴቶች ግርዛትን ሪፖርት አለማድረግ ወይም መፈጸሙን መከላከል ወንጀል ነው። ወንጀሉ በሌላ አገር ቢፈፀም እንኳን ይህ ሰው ለፈጸመው ወንጀል ስዊድን ውስጥ ሊከሰስ ይችላል። ስዊድን ውስጥ የሴት ልጅ ግርዛትን በመፈጸም ወንጀል የሚሰራ ሰው እስከ 10 አመት በሚደርስ እስራት ሊቀጣ ይችላል።

ለበለጠ መረጃ
**konsstympning.se**
ይጎብኙ